ፍኖተ

# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ጥር 27 ቀን 2005 ዓ.ም.
ቁጥር 64

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

## 33ቱ ፓርቲዎች ኢህአዴግን አስጠነቀቁ

3

## የፊቼ ነዋሪዎች የአካባቢው ባለስልጣናት ለህይወታችን ሥጋት ሆነዋል በማለት አማረሩ

6

## መድረክ ማኒፌስቶውን አጸደቀ

3

## የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር ሊቀመንበር በተፈበረከ መረጃ መንግስት ሊያስረው እንደሚፈልግ ገለፀ

### “የኢህአዴግ ስርአት መወገድ አለበት፤ ሙሉ ጊዜዬን ለፖለቲካ ስራ በማዋል ስርአቱን ለመታገል ተዘጋጅቻለሁ”ሀብታሙ አያሌው

ላለፈው አንድ አመት የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር ሊቀመንበር የሆነው ሀብታሙ አያሌው ከአሸባሪ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት እንዳለው በማስመሰል በኢሜልና በስልክ የማያውቃቸው መልዕክቶች እየደረሱት እንደሆነ ለፍኖተ ነፃነት ገለፀ፡፡

በፈጠራ መረጃዎች ብዙዎች እንደታሰሩ ያስታወሰው ሀብታሙ ከዚህ መልዕክት ጀርባ በስውር የሚንቀሳቀሱ የመንግስት የደህንነት ሀይሎች እጅ እንዳለበት እንደሚያምን አስረድቷል፡፡ አያይዞም ያለው ስብዕናና ሀይማኖታዊ አስተዳደግ ከሽብርና ጥፋት ሊያቀራርበው እንደማይችል ተናግሯል፡፡

የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር አባላትን “እንዴት ከሀብታሙ ጋር ትሆናላችሁ እሱ ከ ግንቦት ሰባት ጋር ግንኙነት አለው” በማለት በመንግስት ደህንነት ሀይሎች ሀሰተኛ ውንጀላ እየቀረበብኝ ነው በማለት አስረድቷል፡፡ ጨምሮም የማህበሩ አባላት የመንግስት ካድሬዎችና ደህንነቶችን ሴራ ለማጋለጥ እየተዘጋጁ መሆኑን ገልጧል፡፡

አሁን ባለው የኢትዮጵያ ሁኔታ በሲቪክ ተቋማት ተደራጅቶ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብሎ እንደማያምን የገለፀው ሀብታሙ አያሌው “የኢህአዴግ ስርአር መወገድ አለበት፤ ሙሉ ጊዜዬን ለፖለቲካ ስራ በማዋል ስርአቱን ለመታገል ተዘጋጅቻለሁ” ብሏል፡፡ ከሀብታሙ አያሌው ጋር ያደረግነውን ሙሉ ቃለምልልስ በድረ ገፃችን ላይ ያገኙታል፡፡

## የ33ቱ ፓርቲዎች ቀጣይ እርምጃ ምንመሆን ይገባዋል?

5

## በደብረብርሃን ነዋሪዎች በፖሊሶች የተፈፀመን የመብት ጥሰት አጋለጡ

3


## ህወሓትና የመሰነጣጠቅ አዝማሚያው

4

# የአንድነትን የማይመለከቱ ከንቱ ትችቶች

ሰለሞን ስዩም

የጽሁፌ ይዘት አንድነት ላይ ለምን ተፃፈ አይልም፡፡ እኔም በበኩሌ በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ከሁለቴም ሶስቴ ከፍተኛ የሚባል ትችል ለማውረድ ሞክሬአለሁ፡፡ የሚወቀስበት ጭብጥ ካጣሁ ግን ወይ ዝም እላለሁ፣ አሊያም መደነቅ ያለበት ነገር ሳደንቅ እገኛለሁ፡፡ ለማንኛውም ቆንጆ በተባለች መፅሄት ጥር 2005 ዓ.ም "አንድነት የተቃዋሚዎች ህውሃት?" የሚል ፅሁፍ ተካቷል፡፡ ጸሀፊው "ህውሃት" ሲል "ህወሓት" ለማለት እንደፈለገ ተረድተን እንቀጥል፡፡ የሆነ ሆኖ ርዕስ ስላማረልን ብቻ አንፅፍም፡፡ የቆንጆ መፅሄት ላይ የወጣው የዚህ ጽሁፍ ጭብጥ ሁለት ይመስለኛል፡፡ አንደኛው "የኢትዮጵያ የዘመነ ኢህአዴግ የተቃውሞ ጎራ ውጤት ያላመጣው በትብብሮች ያለመሳካት ነው" የሚል ነው፡፡ ሌላው ጭብጥ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ "አንድነት የተቃውሞው ጎራ ላይ ህወሓት ሆነ" የሚል ነው፡፡ እንግዲህ አንዳንድ የቆንጆ መፅሄት አንቀፆችን እያነሳን እንወያይ፤ ኩኩሽ በተባለ(ች) ስም የሰፈረው ይህ ፅሁፍ "በሀገራችን የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሀያ አመታት የዘለቀው የተቃውሞ መንገዳቸው ለህዝብ ያመጣው ለውጥ ያክል ነው፤ ለዚህ እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚያግባባቸው መንገድ ላይ የተመሰረተ የጋራ እንቅስቃሴ ያለማድረጋቸው ነው" ትላለች፡፡ ቆንጆ ይህ እስከ ዛሬ የዘለቀ እውነታ መሆኑን ትናገራለች፡፡ እውነት ለመናገር የኢትዮጵያ ፖለቲካ ትብብር ያንሰዋል፡፡ እንግዲያውስ ስለ ትብብር የሚያቀነቅን ፓርቲ መፈጠሩ መልካም በሆነ፡፡ አንድነት ፓርቲ ከአንድ አመት ወደዚህ ይህ የትብብር ነገር አስፈላጊ መሆኑን ደርሶበታል፡፡ ግን አክርሮ በመያዝ የሚያስወቅሰው አይመስለኝም፡፡ ገና የሚያኩራራ ደረጃ ላይም አልደረሰምና፡፡ የሆኖ ሆኖ የፓርቲዎች ትብብር እና ውህደት የአንድነት ፓርቲ የቆየ እቅድ መሆኑን ለማወቅ ፓርቲው በጥር 2003 ዓ.ም ያሳተመው የስትራቴጂና የአምስት አመት ዕቅድ መፅሃፍ በሰፊው ያትታል፡፡ በመፅሀፉ ውስጥ ለዚህ ዘርፍ ከስራ አስፈፃሚ የተወጣጡ ኮሚቴ እንደሚዋቀር ይገልፃል፡፡ የጊዜ ሰሌዳም ተይዞለት አፈፃፀሙ የሚገመገም ይሆናል፡፡ የአንድነት ፓርቲ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ኢ/ር ዘለቀ ረዲ፣ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ አቶ ሙላት ጣሰው፣ የኢዲቶሪያል ቦርድ አስተዳደርና ፋይናንስና የድርጅት ጉዳይ ም/ ኃላፊ አቶ ስዩም መንገሻ፣ የብሄራዊ ምክር ቤቱ ፀሀፊ አቶ ትዕግስቱ አወሉ… የዚህ ውጤት ናቸው፡፡ ቆንጆ በኩኩሽ ስም ከዚህ ቀደም የነበሩት ትብብሮች የሚፈርሱት ተቃዋሚዎችን "የተጣባቸው ያለመቻቻል ባህልና አንድ ፓርቲ ራሱን ከሌላው የተለየ አድርጎ የማሰብ ልክፍት የፈጠረው ችግር ነው" ትላለች፡፡ ለዚህ ደግሞ አንድነት ፓርቲ በትብብር ውስጥ እያሳየ ያለው ፀባይ መሆኑን አቶ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ አዲስ ታይምስ ላይ የፃፉትን መረጃ ታደርጋለች፡፡ በመሰረቱ ለአቶ ቡልቻ ሀሳብ መልስ የሰጡት ዘለቀ ረዲ መሆናቸው ከምንም በላይ አስደስቶኛል፡፡ ከአመት በፊት ዘለቀ ረዲ የብርሃን ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ም/ሊ/ መንበር ነበሩ፡፡ ሆኖም ፓርቲያቸው ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ጋር ባደረገው ውህደት ዛሬ በአንድነት ያላቸውን ኃላፊነት ገልጠናል፡፡ ዘለቀም ሆኑ የብርሃን ፓርቲ ፕሬዚደንት የነበሩት አቶ ሙላት ጣሰው ስለውህደት



ሲደራደሩ በቅድሚያ በውህደቱ ውስጥ በሚኖረን ቦታ ላይ እንወያይ አላሉም፡፡ እንዲያውም ኢ/ር ዘለቀ ረዲ ድህረ ውህደት ከዶ/ር ነጋሶ ጋር የሁለቱ ፓርቲዎች የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ባሉበት ለአንድነት ፕሬዚዴንትነት ተወዳድረው ነበር፡፡ ስለዚህ ለአቶ ቡልቻ ምንም አልልም፡ : "Kabajamoo Obboo bulcha, edaa kana kana hinbektan ture? Haata'uu malee yoomi-yyuu isin kabajna" ከማለት በቀር፡፡ ቆንጆ "የበላይ ነኝ የሚለው ፖለቲካ ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች አንድም ቀን ሲበጅ አልተስተዋለም" ትላለች፡፡ በተቃራኒው ግን አንድነት በዚህ ራሱን ለህብረትና ትብብር አሳልፎ የመስጠት ሂደት አንዳንድ አባላቱና ደጋፊዎቹ እንደሚናደዱ አውቃለሁ፡፡ እነዚህ አባላት "ሌሎቹን ለመጠበቅ ወደኋላ ከምንመለስ በያዝነው ፍጥነት ብንቀጥል ምንኛ በተራመድን ነበር" ይላሉ፡፡ በመሆኑም "የአንድነት አዝማሚያ በመድረክ ውስጥ ባሉት በሌሎች አባሎች ማለትም በደቡቦች በኦሮሞዎችና በአረና ላይ የበላይነት ለማሳየት ነው" በሚል ቆንጆ የጠቀሰችው የአቶ ቡልቻ ሀሳብ ከብዥታ የመነጨ ነው፤ አሊያም ያልተገባ ፍርሃት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ማንም ሰው አቶ ቡልቻን ምስጢር አወጡብን አይላቸውም፤ ምክንያቱም እንኳን ምስጢር በግልጥ ያለውን የአንድነት ሀቅ እንኳ አልተናገሩም፤ አሊያም አያውቁም፡፡ በመሆኑም "ሳይቃጠል በቅጠል" ፣ "ስውር አካሄድ" የሚሉ ሀረጋት እዚያው በኢህአዴግ መንደር ቢፈለጉ እላለሁ፡፡ በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ችግር ምን መፍትሄ ይኖረው እንደሆን የተጠየቁት እሸቱ ጮሌ ሶስት የመፍትሄ አሳቦችን ደረጃ በደረጃ አስቀምጠው ነበር፤ 1ኛ ትብብር፣ 2ኛ ትብብር፣ 3ኛ ትብብር፡፡ ለኢትዮጵያ የተቃውሞ ጎራ ከዚህ የተሻለ መንገድ አለ ብሎ አንድነት አያስብም፡፡ በመጨረሻም የቆንጆን ሀሳብ ብናከብርም በጀርመናዊው የፍልስፍና ሰው ሾፐንሀወር አባባል እንደምድም፤ "የምትለው ከሌለህ ዝም በል"- "ቆንጆ" አትዘላብጂ ለማለት ነው፡፡





# 33ቱ ፓርቲዎች ኢህአዴግን አስጠነቀቁ

33ቱ ፓርቲዎች "ኢህአዴግ ስለ አካባቢ ምርጫ የሰጠው መግለጫ የጥያቄዎቻችንን ትክክለኛነትና አግላይ አቋሙን ያረጋገጠበት ነው" በሚል ርዕስ መግለጫ አወጡ፤ ኢህአዴግን አቋሙን እንዲያስተካክልም አስጠነቅቀዋል፡፡

የኢህአዴግ ጽ/ቤት ኃላፊና የምርጫ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ የአቶ ሬድዋን መግለጫ ኢህአዴግ ዛሬም በአገራዊና ህዝባዊ ጉዳዮች ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች በሙሉ ወሳኝም፣ ባለመፍትሔም እኔ ብቻ ነኝ ከሚል የእብሪት ስሜት አለመላቀቁንና ሀላፊነት በጎደለው ጭፍን ጥላቻ እየተነዳ መሆኑን ያመለክታል ያለው የፓርቲዎቹ መግለጫ፤ "ይህ አካሄድ ለማንም የማይጠቅም ከመሆኑም በላይ ብዙ ርቀት ሊያስኬደው እንደማይችል በድጋሚ ሲገለጽ ብቻ ሳይሆን በህዝባዊ ሀይል ሊገታ የሚገባው መሆኑን እንረዳለን" የሚል አሳስቧል ::

ፓርቲዎቹ መግለጫቸው ያቀረቧቸው ጥያቄዎች ቀላል እንደሆኑ አስገንዝቧል: : ጥያቄያቸው ሲጠቃለል መንግስትና ኢህአዴግ ይለያዩ፣የመገናኛ ብዙሀን ፍትሀዊ አጠቃቀም ይኑር፣የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት የመንቀሳቀስ መብት ይከበር፣ምርጫ ቦርድ ከገዥው ፓርቲ ተጽዕኖ ተላቅቆ በነፃነት ይደራጅ!የህግ የበላይነት ይረጋገጥ፣በገዥው ፓርቲ አማካይነት ለ አፈና የወጡ ህጎች ይከለሱ/ይሻሩ፣ በድምሩ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተከብረው የህዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ይረጋገጥ ዘንድ የምርጫ ሜዳው ይስተካከል የሚሉ ናቸው በማለት የጥያቄዎቹን ዘርዝረዋል፡፡ የኢህአዴግ አቋምና አካሄድ የትም አያደርሰውም ማንንም አይጠቅምም በማለት አስጠንቅቀዋል፡፡ 33ቱ የአዳማ ፔቲሽን ፈራሚ ፓርቲዎች ጥር 26 ቀን 2005 ዓ.ም ህዝባዊ ስብሰባ ለማድረግ ቢያቅዱም የመሰብሰቢያ አዳራሾችን እንዳያገኙ በመንግስት ጫና እየተደረገባቸው በመሆኑ ስብሰባውን ለማራዘም መገደዳቸው ታውቋል፡፡

# መድረክ ማኒፌስቶውን አጸደቀ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) 7ኛ መደበኛ ጉባኤውን አደረገ፡፡ ጉባኤው የተሻሻለውን ማኒፌስቶ አጽድቆ ከዚህ በፊት በዙር ይደረግ የነበረው የመድረክ ሊቀመንበር ምርጫ በውድድር በድምጽ ብልጫ እንዲመረጥ የተወሰነ ሲሆን የግንባሩን መተዳደሪያ ደንብ በስራ አስፈፃሚ ደረጃ ተጨማሪ ውይይት እንዲደረግበት ስምምነት ላይ በመድረስ እንዳፀደቀው ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው መረጃ ያመለክታል፡፡

የዜና ምንጮቻችን አንደገለጹልን ከስብሰባው በፊት ተዘጋጅቶ በቀረበው ረቂቅ ማኒፌስቶ ላይ ውይይት ተደርጎ ሰፊ ማሻሻያ ከተደረገበት በኋላ እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በፊት በመድረክ ውስጥም ሆነ በህብረተሰቡ ዘንድ ቅሬታ ሲያስነሳ የነበረው የመድረክ አመራር በተራ ወይም በዙር እንዲዳረስ የተደረገው አሰራር ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ጠቅላላ ጉባኤው ሰፊ ውይይት አድርጎበት በውድድር ብቃት ያለውና አብላጫ ድምጽ ያገኘ ሊቀመንበር ሆኖ እንዲሰራ ተወስኖዋል፡፡ ሌላው የቀረበው አጀንዳ መተዳደሪያ ደንቡ ነበር ፡፡ ጉባኤው ላይ በተሻሻለው ረቂቅ ደንብ ላይ ጠንካራና አከራካሪ ነጥቦች ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ በመጨረሻም ጉባኤው እየተግባባበት ተጉዞዋል፡፡ ይሁን እንጂ ደንቡ እንደገና በዝርዝር መታየት እንንደሚገባው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ለዚሁ ሲባል በመተዳደሪያ ደንቡ ለሌላ ተጨማሪ የውይይት ጊዜ ተላልፏል ፡፡ መድረክ ያፀደቀው ማኒፌስቶ የኢህአዴግን መሰረታዊ ስህተቶች የገመገመና አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦችንም ያካተተ ነው፡፡

ግንባሩ በጠቅላላ ጉባኤውና ባፀደቃቸው መተዳደሪያ ደንብና ማኒፌስቶ ላይ በቅርቡ መግለጫ እንደሚሰጥም ለማወቅ ተችሏል፡፡

# በደብረብርሃን ነዋሪዎች በፖሊሶች የተፈፀመን የመብት ጥሰት አጋለጡ

በአማራ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ዋና ከተማ በሆነው ደብረብርሃን ከተማ ፖሊስ በነዋሪዎች ላይ የመብት ጥሰት እየፈፀመ መሆኑ ተጠቆመ፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች ዝግጅት ክፍላችን ድረስ በመምጣት በሰጡት መረጃ ፖሊስ በፀጥታ ማስከበር ስም በወንጀል ድርጊት ላይ መሰማራቱን አጋልጠዋል፡፡ ነዋሪዎቹ እንደሚሉት ፖሊስ ራሱን ከህግ በላይ አድርጐ ስለሚቆጥር የዜጐችን ህገመንግስታዊ መብት በሚጥስ አሰራር ላይ ተሰማርቷል፡፡ ነዋሪዎቹ ጨምረው እንደሚያስረዱት "ፖሊሶች ከካድሬና ከደህንነት በሚሰጣቸው ትዕዛዝ ንፁሐን ዜጐችን በፖለቲካ አመለካከታቸው እያስጠሩ ያሸማቅቃሉ፣ ያስፈራራሉ፣ ይደበድባሉ፣ ያስራሉ፡፡" ነዋሪዎቹ በምሳሌነት ሲገልፁም "የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም ከቀበሌው ኮሚኒቲ ፖሊስ፣ ከወረዳው ፖሊስ፣ ከክልሉ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ እና ከፌዴራል ፖሊስ የተውጣጣ ቡድን ከለሊቱ 8 ሰዓት ቀበሌ 06 ቀጠና 4 ውስጥ የጌታ ወ/ ሚካኤል የተባሉን ግለሰብን ግቢ ከበቡ፡ : የግቢው ነዋሪዎች ለአካባቢው ነዋሪ በስልክ በማሳወቃቸው የአካባቢው ህዝብ ወጥቶ ምንድነው? ብሎ ጠየቀ፡ : እዚህ ግቢ የሚኖር አቶ አበበ በቀለ የተባለ ግለሰብ አካባቢውን በጥብጧል የሚል መረጃ ደርሶን ነው ብለው መለሱ፡ : የመላው አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ የሰሜን ሸዋ ተጠሪ የሆኑት አቶ አበበ ከነጐረቤቶቹ በሠላም ተኝቷል፡፡ በአካባቢው የተፈጠረም የፀጥታ መጓደል የለም፡፡ ማነው እንዲህ ብሎ የነገራችሁ በዚህን ሰዓት ከተለያየ ቦታ የተውጣጣ ፀጥታ አስከባሪዎችስ እንዴት ተቀናጅታችሁ ልትመጡ ቻላችሁ ብለን ብንጠይቃቸው መልስ ሳይሰጡ አቶ አበበንና ለፖሊሶቹ ጥያቄ ያቀረቡትን ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱ፡፡ የፍ/ቤት ትዕዛዝን ብንጠይቅ ምን አገባችሁ፡፡ የመጠየቅ መብት የላችሁም አሉን፡፡ ለሊቱኑ ለተለያየ ሚዲያ ደውለን በማሳወቃችን ንጋት ላይ በ12 ሰዓት ስትጠሩ ትመጣላችሁ ብለው ታሳሪዎቹ ለቀዋቸዋል" ብለዋል፡ : ታሳሪዎቹ "የታሠርንበት ወንጀል ይነገረን፤ የከሰሰን ሰው ማነው" ብለው ቢጠይቁም መልስ እናዳለገኙ መረጃ ሰጪዎቻችን ጠቁመውናል፡፡ ያለ አንድ ምክንያት ዜጐችን በአመለካከታቸው ለማዋከብና በሐሰት ለመወንጀል ሲባል የአካባቢው ህዝብ ሠላም ማጣቱም እንዳሳዘናቸው ተናግረዋል፡፡ በጉዳዩ ላይ የቀበሌው ኮሚኒቲ ፖሊስ አስተያየትእንዲሰጥበት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም፡፡ ይሁን እንጂ የወረዳውን ፖሊስ አዛዥ ኢ/ር ምንውዬለትን በስልክ አግኝተን ጠይቀናቸው ጉዳዩን አጣርተው እንደሚደውሉ ቢነግሩንም ዜናው እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ምላሽ አልሰጡንም፡፡

# ህወሓትና የመሰነጣጠቅ አዝማሚያው

ዳዊት ሰለሞን

ትግራይን የማስገንጠል ራዕይ በመሰነቅ ዱር ቤቴ ብለው የነበሩት የህወሓት ፋኖዎች የትግራይ ህዝብ ከኢትዮጵያ ተነጥሎ መኖር እንደማይችልና ይህንንም አጀንዳቸውን ሊያስፈፅምላቸው እንደማይችል ሲገነዘቡ "የትግራይ ሪፐብሊክን" የመመስረት አጀንዳቸውን ወደ መዝገብ ቤት በመመለስ ኢህአዴግን መሠረቱ የኢህአዴድ፣ ብአዴንና የደቡብ ህዝቦችን ይወክላሉ የተባሉ ድርጅቶች (በህወሓት ይሁንታ) ከተማረኩ የደርግና የኢህአፓ ወታደሮች አማካኝነት መመስረታቸውንና ግምባሩን መፍጠራቸውን የሚናገሩ ተንታኞች በሦስቱ ድርጅቶች ውስጥ ለአመታት ህወሓት የብረት ጡንቻ እንደነበረው የተለያዩ ዋቢዎችን በመጥቀስ ይሞግታሉ። የህወሓት ከፍተኛ አመራሮች ግን በአንፃሩ ተጠፍጥፈው (ህወሓት የሚፈልገውን አይነት ቅርፅ) እንዲይዙ ተደርገዋል ከሚባሉት ድርጅቶች በተሻለ የተለያዩ ሃሳቦችን በማንሳት የመወያየት ያልጣማቸውን ውሳኔ የመቃወም መብት እንደነበራቸው የሚናገሩ ብዙዎች ናቸው። ከህወሓት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል በዛ ያለ ቁጥር የነበራቸው ኤርትራ እንደ አገር ከታወቀች በኋላ የኢትዮጵያ የጡት ልጅ በመሆኗ ያለገደብ ተጠቃሚ መሆኗ ያበሳጫቸው ነበር። በ1993 ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የነበረው ልዩነት ገሃድ ወጥቶ ህወሓት ለሁለት ተሰነጠቀ። ለፍኖተ ነፃነት ኦን ላይን ሚዲያ ቃለ ምልልስ የሰጡት አንጋፋው የህወሓት ታጋይ አቶ ስብሃት ነጋ "ህወሓት በታሪኩ ተሰንጥቆ አያውቅም። ተፈጠረው ልዩነት ደስተኛ ያልነበሩ አባላት ድርጅቱን ለቅቀው ወጡ እንጂ መሰንጠቅ የሚባል ነገር አልተፈጠረም" ብለዋል። እነ ስዬ አብርሃን ተከትለው የወጡት የህወሓት ነባር ታጋዮች፣ ህወሓት ውስጥ በቀሩት የእነ መለስ ዜናዊ ቡድን "እንደ ከሃዲ" ሲቆጠሩ እነርሱም በተራቸው "ተንበርካኪ" በማለት አንዳቸው ሌላኛቸውን ሲያወግዙ ታይተዋል። ስዬም በሙስና ተጠርጥረው ከእነ ቤተሰቦቻቸው ዘብጥያ እንዲወርዱ ተደርገዋል። "እስከ አናቴ በስብሼ ነበር" በማለት ከስንጥቁ በኋላ አፈር ልሶ መነሳቱን የሚናገረው ኢህአዴግ በተሀድሶ መጠነኛ ለውጥ ካደረገ በኋላ መለስ እስከ ሞቱበት ጊዜ ድረስ ጤናማ ድርጅት መስሎ መጓዝ ችሎ ነበር።

ይህ ቡድን በቅርቡ በመቀሌ ባደረገው ስብሰባ የህወሓትን መካከለኛና ዝቅተኛ አባላት በመሰባሰብ የእነ ስብሀትን ሐሳብ ለማንኳሰስ ቢጥርም ተሰብሳቢው ሰዎቹ የተጣሉት ከእናንተ ጋር እንጂ ከእኛ ጋር ባለመሆኑ ወደ ድርጅቱ መመለስ ይኖርባቸዋል" የሚል ምላሽ ማግኘቱ ተሰምቷል።

## የመለስ ሞት የህወሓት ለስላሳ ሞት?

መለስ የህወሓት ሊቀመንበርነትን ከስብሃት ነጋ እጅ ከተቀበሉባት ሰዓት አንስቶ ግብአተ መሬታቸው እስኪፈፀም የድርጅቱ ሁሉም ነገር ነበሩ። ቀሪዎቹ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች ምን ሲሰሩ እንደከረሙ ለማንም ግልጽ ባይሆንም መለስ የህወሓት ኢህአዴግ ጭንቅላት እንደነበሩ በለቅሶው ሰሞን በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ያሉ ቱባ የኢህአዴግ አመራሮች ሲናገሩ መመልከታችን አይዘነጋም። "ከመለስ በኋላ ህወሓት በኢህአዴግ ውስጥ የነበረውን የበላይነት በማስጠበቅ ሊያስጉዘው የሚችለው ማን ነው?" የሚል መሠረታዊ ጥያቄ አመራሮቹን ከስብሰባ ስብሰባ እየተከተለ በውጥረት እንዲከርሙ አድርጓቸዋል። "መለስም ተተኪውን ባለማዘጋጀቱ ለዚህ ክፍተት ተጠያቂ መሆን ይገባዋል።" የሚሉ ድምፆች ከመደመጣቸው ባሻገር "መፍትሔው ከዚህ ቀደም የተሰናበቱ አባላቶቻችን እንዲመለሱ ማድረግ ነው።" እስከ ማለት ተደርሷል። ምንም እንኳን የህወሓት ነባር ታጋዮች "አቦይ" (አባት) በማለት የሚጠሯቸው አቶ ስብሃት ነጋ ራሳቸውን ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት ቀደም ብለው ያገለሉ ቢሆንም በጭንቅ ሰዓት ማዕከላዊ ኮሚቴውን "ቤታቸው" በማድረግ ከመፍትሄ አፈላላጊዎቹ ዋነኛው እንደነበሩ ምንጮቻችን ይገልፃሉ። "ህወሓትን ከጀርባ ይዘውሩታል፤" የሚባሉት አቶ ስብሃት የቀድሞዎቹ አመራሮች ወደ ድርጅቱ ይመለሱ የሚለውን ሐሳብ ማራመድ መጀመራቸው ለጉዳዩ ክብደት እንድንቸረው ያደርገናል። አቦይ ስብሃት በቅርቡ ለ "ኢቲዮ ምህዳር" ጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ ከህወሓት የወጡት ሰዎች የአካሄድ እንጂ የፕሮግራም ልዩነት ከህወሓት ጋር እንደሌላቸው መናገራቸው አይዘነጋም። የአቦይን "ወንድሞቻችን ይመለሱ፤" የሚል ሀሳብ በጽኑ የተቃወሙ ደግሞ በአቦይ ፀሐዬ ዙሪያ መሰለፋቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህ ቡድን በቅርቡ በመቀሌ ባደረገው ስብሰባ የህወሓትን መካከለኛና ዝቅተኛ አባላት በመሰባሰብ የእነ ስብሀትን ሐሳብ ለማንኳሰስ ቢጥርም ተሰብሳቢው ሰዎቹ የተጣሉት ከእናንተ ጋር እንጂ ከእኛ ጋር ባለመሆኑ ወደ ድርጅቱ መመለስ ይኖርባቸዋል" የሚል ምላሽ ማግኘቱ ተሰምቷል። በእነ አባይ ወልዱ ይደገፋል የተባለው ቡድን ለተወሰኑ የድርጅቱ ተፅእኖ ፈጣሪ አመራሮችና አባላት በተነው በተባለው ወረቀትም ከድርጅቱ የተሰናበቱ ሰዎች በየትኛውም መንገድ ወደ "እናት" ድርጅታቸው መመለስ እንደማይገባቸው አጽንኦት በመስጠት አባላቱ "በመለስ መንገድ" ድርጅቱን ለማዳን እንዲንቀሳቀሱ ጠይቋል። የቀድሞዎቹን የህወሓት ታጋዮች ወደ ድርጅታቸው የመመለስ እንቅስቃሴ መለስ አልጋ ላይ መዋላቸው ከተነገረባት ቅጽበት አንስቶ ውስጥ ውስጡን በአቶ ስብሃት ነጋ አማካኝነት ስካሄድ እንደነበረ የሚጠቅሱ ምንጮች ይህንኑ እንቅስቃሴ ለማኮላሸት በማሰብ አንደኛው ቡድን(የእነ አቶ አባይወልዱ መሆኑ ነው) ለህዝብ ይፋ ሳይደረግ የቆየውን እነ ስዬ አብርሃ መለስ ይመሩት የነበረውን ስብሰባ ረግጠው ሲወጡ የሚያሳይ ቪዲዮ በዩቲዩቡ አማካኝነት መልቀቃቸውን ያስታውሳሉ። በቪዲዮው ላይ መለስ ድርጅቱን ለማዳን ቀሪዎቹ አባላት ጠንክረው እንዲሰሩ ለማፀኑ ይታያሉ። ህወሓት በመጪው የካቲት 11 የምስረታ በሚሉን ያከብራል የኢህአዴግ ጠቅላላ ጉባኤም በዚህ ወቅት ይደረጋል። አሁን የተለኮሰው የልዩነት እሳት በክብረ በአሉና በስብሰባው ወቅት ጥርስና እግር ተበጅቶለት አካል ሠርቶ ሊታይ እንደሚቻል የሚተነብዩ ብዙዎች ናቸው። እስከዛው ግን ሁሉን ነገር ምስጢር በማድረግ ማቆየት የሚፈልገው ህወሓትን የሚያፈተልኩ መረጃዎችን ከዳር ሆነን መቃረማችንን እንቀጥላለን።





# የ33ቱ ፓርቲዎች ቀጣይ እርምጃ ምንመሆን ይገባዋል?

ነብዩ ኃይሉ

ህዳር 4 በወጣችው ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ላይ "ምርጫ ለለውጥ ወይስ ከአምባገነኖች ጋር ለመደነስ?" በሚል ርዕስ ሀቀኞቹ ተቃዋሚዎች ውጤቱ አስቀድሞ ወደታወቀ ምርጫ ከመግባት እንዲቆጠቡ በማሳሰብ፤ ለአንድ ምርጫ ውጤታማነት የሚያስፈልጉ መሰረታዊ የሆኑ የቅድመ ምርጫ መደላድሎች (ለመራጮች ትምህርት የሚሰጡ ጠንካራ የሲቪክ ማህበራት መኖር፣ ለውድድር የሚቀርቡት ተፎካካሪዎች የምርጫ ቅስቀሳ የሚያደርጉበትና ህዝባዊ ስብሰባዎችን የሚያደራጁባቸው ሁኔታዎች ምቹ መሆን፣ አድሏዊ ያልሆነ የመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀም መኖር፣ ግልፅነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን የምርጫ አስፈፃሚ አካልና ስርአት መኖር እንዲሁም በምርጫው ላይ የሚፈጠሩ ቅሬታዎችንና አለመግባባቶችን ያለአድሎ መፍታት የሚያስችል አካልና ስርአት) እንዲፈጠሩ መንግስት ላይ ጫና ማድረግ እንደሚገባቸው ጽፌ ነበር። ከወራት በኋላ 33ቱ የአዳማ ፔቲሽን ፈራሚ ፓርቲዎች ምርጫው ለሁሉም ወገን ምቹ እንዲሆን፣ ምርጫ ቦርድና መንግስት ሊመልሷቸው ይገባሉ ያሏቸው ባለ 12 ነጥብ ጥያቄዎች ባለመመለሳቸው በምርጫው እንደማይሳተፉ አስታውቀዋል።

በአሁኑ ጽሁፌ ደግሞ ከምርጫ መውጣት ብቻውን መፍትሔ እንዳልሆነና ፓርቲዎቹ ጥያቄዎቻቸው ተመልሰው ዳግም ምርጫ እንዲጠራ በገዢው ቡድን ላይ በተለያዩ ሰላማዊ ተቃውሞዎች ጫና ማድረግ እንደሚገባ ለመጠቆም እሞክራለሁ።

እንደ ኢህአዴግ ያሉ አምባገነን መንግስታት ምርጫን የህዝብን ሉአላዊ የስልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ እንደማይጠቀሙበት የታወቀነው። በመሆኑም ስልጣናቸውን በማያሳጣቸው አግባብ ለወጉ ያክል የውሸት ምርጫ እንዲካሄድ ያደርጋሉ። ኢህአዴግም የስልጣን ሽግግር የማይደረግበት የፌዝ ምርጫ በማድረግ የሚስተካከለው የለም።

በመሰረቱ 33ቱ ፓርቲዎች በፌዝ ምርጫ ላለመሳተፍ ያስተላለፉት ውሳኔ ትክክለኛ ነው። የፓርቲዎቹን ከምርጫ መውጣት ተከትሎ፣ በምርጫው እስከአሁን ከኢህአዴግ ውጪ አንድም ፓርቲ ዕጩ አለማስመዝገቡና አብዛኛው ህዝብ በግዳጅ የምርጫ ካርድ እንዲወስድ መገደዱ በዚህም ከፍተኛ ቅሬታ መፈጠሩ፣ ምርጫው ኢህአዴግ ብቻውን የሚሮጥበት እንደሆነ ያሳየበት ነው። ይህም ምርጫው ከአሁኑ ቅቡልነት(legitimacy) እያጣ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ነው። ይህ ሁኔታ እጅግ ያሳሰበው ኢህአዴግ በጽ/ቤት ኃላፊውና የምርጫ ኮሚቴው ሰብሳቢ በሆኑት አቶ ሬድዋን ሁሴን በኩል አነጋጋሪ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቶ ነበር። በዚህ መግለጫው በምርጫው አንሳተፍም ያሉትን 33ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከመተቸት አልፈው ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ በምርጫው ተሳተፉ አልተሳተፉ የሚጨምሩትም፤ የሚቀንሱትም ነገር የለም የሚል ኃይለቃል ሰንዝረዋል።

ይህ የሰውየው ንግግር የኢህአዴግን ዕብሪት አጉልቶ ያሳየ ይመስለኛል፤ ፓርቲው ባለፉት 21 አመታት ራሱን በሀገሪቱ ጉዳይላይ አድራጊ ፈጣሪ በማድረግ በሀይል ሰይሟል። ሌሎች ፓርቲዎችም ሆኑ በሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል የሚል አካልን ፋይዳ ቢስነት በአደባባይ በዕብሪት በማናናቅ ይጠመዳል። ሆኖም ተፎካካሪ ፓርቲዎቹ ተጠናክረው ሲመጡ ጨዋታውን ይቀይረዋል፤ ፓርቲዎቹን በህገወጥነትና መክሰስ፣ ህዝባዊ መሰረታቸው ካስፈራው ደግሞ ወደ ድርድር መሳብ ይጀምራል።

ይህ የሚያሳየን የኢህአዴግና የባለስልጣናቱ የዕብሪት መግለጫዎች የተፎካካሪዎቻቸው የማስገደድና ተፅእኖ የማሳደር አቅም ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቁርጠኛ ሆነው በህብረት መቆም ከቻሉ ያለጥርጥር ኢህአዴግን ማስገደድ ይችላሉ። በአዳማ የተፈጠረው የ33 ፓርቲዎች መሰባሰብ ደግሞ አንድነቱ ተጠብቆ እስከዘለቀ ድረስ ተስፋ ሰጪ ነው። ፓርቲዎቹ ካወጧቸው መግለጫዎች መረዳት እንደሚቻለው፣ ፓርቲዎቹ ራሳቸውን ከምርጫው አግልለው መቀመጥን የመረጡ አይመስሉም። ይልቁኑም ህዝቡ በፌዝ ምርጫዎች እንዳይሳተፍ ጥሪዎችን በማስተላለፍ፣ ህዝባዊ ስብሰባዎችን ለመጥራት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ።

በእስካሁኑ ተሞክሮ እንደታየው ግን አምባገነኑ የኢህአዴግ ስርአት ተቃዋሚዎች እንኳን እንደዚህ አይነቱወግዙፍ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ህዝብን እንዲያወያዩ ይቅርና፣ በውቅታዊ ጉዳዮች ላይም እንዳይወያዩ አዳራሽ እንዳያገኙ መሰናክሎችን ያስቀምጣል።

እነዚህን መሰናክሎች አልፎ ውጤት ላይ ለመድረስ የፓርቲዎቹ ቁርጠኝነትና ህዝቡን ለማነቃነቅ አቅም ወሳኝ ነው። 33ቱን ፓርቲዎች ከሚያስተባብሩት የኮሚቴ አባላት መረዳት እንደሚቻለው ለጥር 26 ተጠርቶ የነበረው ህዝባዊ ስብሰባ "በአዳራሽ እጦት" ተራዝሟል። ሁኔታዎች በዚህ እንዳይቀጥሉ ፓርቲዎቹ አማራጫችን ብለው የያዙት ህዝባዊውን ስብሰባዎቹን በየፓርቲዎቹ ጽ/ቤት ውስጥ ማድረግን ነው። የኢህአዴግ ፍላጎትም ይኸው ይመስለኛል፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከጽ/ቤታቸው ወጥተው ህዝብን እንዲያገኙ አይፈልግምና።

የአዳራሽ ህዝባዊ ስብሰባዎች ይልቅ የአደባባይ ስብሰባዎች የተሻለ ተሳታፊ ለማሳተፍ ያስችላሉ። ይህም የሚሆነው ስብሰባውን ጉዳዬ ብሎ ከሚመጣው ታዳሚ በተጨማሪ አላፊ አግዳሚውም የስብሰባውን መልዕክት እንዲሰርሰው ማስቻሉ ነው። በመሆኑም ከትላልቅ አደባባዮች እስከ መንደር ሜዳዎች ተጠቅሞ ህዝብን በቅርበት ማግኘት በአዳራሽ ወይም በፓርቲዎች ጽ/ቤት ከሚደረጉ ስብሰባዎች ይመረጣል። ከስብሰባዎቹ አስቀድሞ የስብሰባውን አላማ የሚያስረዱ በራሪ ወረቀቶችን በስፋት መበተን፣ እንዲሁም ስብሰባዎቹን በተከታታይ በተለያዩ ቦታዎች ማድረግ መልዕክቱ ህዝቡ ዘንድ እንዲዘልቅና ጥያቄው ህዝባዊ መሰረት እንዲይዝ በማድረግ ረገድ ፋይዳው የጎላ ነው።

ከዚህ ጎን ለጎን ፓርቲዎቹ ያቀረቧቸውን መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች በሚመለከቷቸው መንግስታዊ አካላት አለመመለሳቸውን እንደ አንድ የተቃውሞ ማድረጊያ ነጥብ መጠቀም ያስፈልጋል። በመሆኑም 12ቱ ጥያቄዎች እንዲመለሱ መንግስትን ለማስገደድ፣ ጥያቄዎቹ በሚመለከቷቸው የመንግስት መስሪያቤቶች(በምርጫ ቦርድ፣በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና በፍትህ ሚ/ር) ደጃፍ ላይ በአነስተኛ ቁጥር(በፓርቲ አመራሮችና አባላት) ተጀምሮ ወደ ህዝባዊ ተቃውሞ የሚያድግ እንቅስቃሴ ማድረግ ኢህአዴግ ከዕብሪት እንቅልፉ እንዲነቃና ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጥ ያስገድደዋል። ይህም 33ቱን ፓርቲዎች ወደ ተፅእኖ ፈጣሪነት ያሸጋግራቸዋል።

# የፊቼ ነዋሪዎች የአካባቢው ባለስልጣናት ለህይወታችን ሥጋት ሆነዋል በማለት አማረሩ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን መስተዳድር በግራር ጀርሶ ወረዳ የቦንያ አኖ ጊኖ ቀበሌ ነዋሪዎች የአካባቢው ኃላፊዎች በጋራ ተመሳጥረው የደህንነታችን ሥጋት ሆነውብናል ሲሉ በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍላችን አስታወቁ፡፡

ነዋሪዎቹ በተደጋጋሚ በስልክና በአካል ዝግጅት ክፍላችን ድረስ በመምጣት እንዳስታወቁት "በአካቢያችን በሠላማዊ ዜጎች ላይ ግድያ ይፈፀማል፡፡ ቤትና ንብረት ይቃጠላል፡፡ ህገወጥ እስርና ድብደባ ይፈፀማል፤ ዛቻ እና ማስፈራራት ይፈፀማል፡፡ ይህንን ድርጊት የሚፈጽሙት ፀጥታ ሠራተኞች፣ የአካባቢ ሚኒሻ፣ ፖሊስና ካድሬ የሚባሉት ናቸው፡፡

ህገወጥ ድርጊቱን ሲፈፀም ለፖሊስም እና ለአካባቢ አስተዳዳሪዎች አቤቱታ ሲቀርብላቸው በፌዝ እንዲህ ዓይነት ድርጊት ተፈፀመ እንዴ? በማለት ያላግጣሉ" በማለት አማረዋል፡፡ ነዋሪዎቹ ተፈፀመ ያሉትን ድርጊት በዝርዝር ሲያስረዱ "ከዚህ በፊት የቀበሌአችን ነዋሪ የሆነው አቶ ቸሩ ዘውዴ በአደባባይ በታጣቂዎች ተገሎ፤ ገዳይም አስገዳዮችም ላይ እርምጃ አልተወሰደም፡፡ ግድያውን ያቀነባበሩ የቀበሌውና የወረዳው ባለሥልጣናትም ለፍርድ አልቀረቡም፡፡ በዚሁ ሳምንት የሚችን የ85 ዓመት ወላጅ አባቱና የ75 ዓመቱ እናቱ ያሉበትን ቤት ለሊት በእሳት ተለኮሰ፤ የአካባቢው ነዋሪ እንዳያጠፋ በቤቱ አካባቢ ምንነቱን ያላወቅነው ፍንዳታ ተሰማ፡፡ የአካባቢው ህዝብ ፍንዳታውን ከሰማ በኋላ እሳቱን ከማጥፋት ተቆጥቦ ቤቶቹ ከነንብረታቸው በእሳት ወድመዋል፡፡ ይህ ሁሉ ሲፈፀም ፖሊስም ሆነ በየደረጃው ያሉ አስተዳዳሪዎች አንድም እርምጃ አልወሰዱም፡፡ እንዲያውም ወንጀለኞቹ ለፍርድ እንዳይቀርቡ ይከለከላሉ፡፡

አቤቱታ አቅራቢና ማስረጃ እንዳይቀርብ ተግተው እየሠሩ ነው፡፡ የሚመለከተው የመንግስት አካል ፍትህ እንዲሰጠን እና የደህንነት ጩኸታችንን አሰሙልን ሲሉ" በለቅሶና በምሬት ተናግረዋል፡፡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት የግራር ጀርሶ ወረዳ ፖሊስ ደውለን ጠይቀናቸው ነበር፡፡ ጉዳዩን ከሰሙ በኋላ መልስ ለመስጠት ፍቃደኛ ሳይሆኑ ስልኩን ዘግተውብናል፡፡ የወረዳውን አስተዳዳሪ አቶ ዳንኤልን ለማግኘት በተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም ልናገኛቸው አልቻልንም፡፡ የወረዳውን አስተዳደር ኃላፊ የሆኑትን አቶ ደጀኔን በተደጋጋሚ በስልክ አግኝተናቸው አነጋግረናቸዋል፡፡

አቶ ደጀኔ በመጀመሪያው ቀን ስለዚህ ጉዳይ ምንም መረጃ እንደሌላቸው ጠቅሰው አጣርተው በሚቀጥለው ቀን መረጃ እንደሚሰጡን ቃል ገብተውልን ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት በማግስቱ ስንደውል የወረዳው አስተዳዳሪ አቶ ዳንኤል "በጉዳዩ ላይ እኔ መልስ እሰጥበታለሁ የእናንተን ተንቀሳቃሽ ስልክ ሰጡኝ" ብለው የወሰዱ ቢሆንም ወደ ዜናው እስከተሰራጨበት ሰዓት ድረስ አቶ ዳንኤል ሊደውሉልን ባለመቻላቸው ሀሳባቸውን ማካተት አልቻልንም፡፡

ለፍኖተ ነፃነት መረጃውን የሰጡ ነዋሪዎች እንዳረጋገጡት የወላጆቻቸው ቤት እንዲቃጠል የተደረገባቸውና ወንድማቸው የተገደሉባቸው አቶ ኮራ ዘውዴ የሚባሉ ግለሰብ ናቸው፡፡ አቶ ኮራ ዘውዴ አንድነትን ወክለው ለፓርላማ የተወዳደሩ መሆኑ ይታወሳል፡፡ በሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ እየደረሰ ያለውም ጉዳት በፖለቲካ አመለካከታቸው ላይ የተመሰረተ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቹ ተናግረዋል፡፡

